ቁርስዎን ያዘጋጁ ወይም ቡን ይጠጡ
ያሉንን ቅርሶች ወይም መረጃዎች ይጠቀሙ
መጥተው በመዝናኛ ጊዜዎ ይዝናኑ

የቤተሰብ መገልገያ ማዕከል የሚከፈተው
ከሰኞ እስከ ዐርብ
ከሦስት ሰዓት እስከ አስራ አንድ ሰዓት
(9 AM-5:00PM)
First floor, Main Building
(ከኬሚስቱ በስተጀርባ በግራ በኩል ይታጠፋ)
Royal Children’s Hospital

**የቤተሰብ መገልገያ**
Royal Children Hospital Flemington Road
Parkville Victoria 3052
**ስልክ** 03 93454662 **ፋክስ** 03 9345 4661
**ኢሜይል** frc@rch.com.au
**ዌብሳይት** www.rch.org.au/frc

Family Resource Centre Amharic

# የቤተሰብ መገልገያ ማዕከል

## የቤተሰብ መገልገያ ማዕከል

የቤተሰብ መገልገያ ማዕከል ከሆስፒታሉ ክሊኒክ የ
ተለየ ለቤተሰብና ለተመላላሽም ሆነ በሆስፒታሉ ው
ስጥ ላሉ የበሽተኛ አስታማሚዎች የተዘጋጀ ነው።
ከሆስፒታሉ ጫጫታና ጭንቀት የራቀ፥ ነገር ግን
በሆስፒታሉ ውስጥ ለቤተሰብ ጸጥተኛ ሰላማዊና የ
ሚያዝናና ቦታ ነው።

ማዕከሉ በስፖንሰሮቻችን በብሉ ዴይና አንክል ቦብ
ክለብ መልካም ልግስና በ2003 ዓ ም ተከፈተ።
የአባዛኛዎቹ ለጋሾች ስም በደጋፊዎቻችን ግድግዳ
ላይ በማዕከሉ ውስጥ ሰፍሯል።

በቤተሰብ መገልገያ ማዕከል የመገልገያው ኃሳብና
ዕቅድ በወላጆች የሚመራ ሲሆን ከተገልጋዮችም በየ
ጊዜው አስተያየትን የሚጠይቅ ነው። ቤተሰቦች ራሳ
ቸውን ችለው አገልግሎቱን ለመጠቀም እንዲችሉ
እናበረታታለን። እርስዎም አስተያየትና ስለአገልግሎ
ቱ ያሎትን ኃስብ ማቅረብ ይችላሉ።

የማዕከሉ ቀን በቀን ስራ በፈቃደኞች ላይ የተመረ
ኮዘ በመሆኑ የሚያደርጉት ርዳታ የታወቀና የተመሰ
ገነ ነው።

የቤተሰብ መገልገያ ማዕከል ከህጻናት ከጤንነት መ
ረጃ ማዕከል፣ የRCH ደህንነት ፕሮግራም፣ የሶሻል
ዎርክ ድርጅትና የRCH ትምህርት ኢንስቲቱት
ጋር በቅርቡ የተያያዘ ነው።

## የቤተሰብ መገልገያ ማዕከል የሚሰጠው

- የእንግዳ ማስተናገጃችን ፈቃደኛ የሆኑ ሰራተኞች
  አቅጣጫን የሚያሳየበት፤ ስለአገልግሎቱ ርዳታ
  ና ድጋፍ የሚሰጡበት
- ጽጥተኛና ምቹ የሆነ የወላጆች ክፍል ለመዝናኛ
  ለማረፊያና ለማንበቢያ
- የብዙ ክንውን መሰብሰቢያ ክፍል ለድጋፍ ግሩ
  ፖችና ከሶሻልዎርከር ወይም ከሌላ ሰራተኛ ጋር
  በመሆን ብቻቸውን መገናኘት ለሚፈልጉ ቤተሰ
  ቦች በቅድሚያ ማስመዝገብ ይቻላል።
- ለሴንተርሊክ ሰራተኞች መገልገያ (በቀጠሮ ብቻ)
- ለቤተሰቦች ለብቻቸው ስለ ልጃቸው ጤንነት
  ወይም ስለቤተሰብ ጉዳይ ለመነጋገር የሚያገለግ
  ል ጸጥተኛ ክፍል።
- ለታወቁና የተለዩ የበሽታ ዓይነቶች፥ ስለ አካለ
  ጎደሎና ስለአሳዳጊነት በቂ የሆኑ የማገናዘቢያ መ
  ጽህፍትና ለመረጃና ለማየት የሚያገለግሉ ቢዲዮ
  ዎች መገልገያ ክፍል
- የንግድ ማዕከል፤ የኢንተርኔት፥ የኢሜይል፥ የፎ
  ቶኮፒና የፋክስ መላኪያን መቀቢያ
- የቀላል ምግብ ማዘጋጃ ማዕድቤት። ቡናና ሻይን
  የመሰሉ መጠጦች እንሰጣለን።
- ጠረጴዛና ወንበር ያለው የመመገቢያ ቦታ፥ ባሻ
  ገር የልጆች መጫወቻ ያለው
- ለታካሚዎች ጋደም የሚሉበት ወይም አርፈው
  በቧንቧ የሚመገቡበት የግል ትናንሽ ክፍሎች
- ውጭ በጸጥታ የመቀመጫ ቦታ
- የግል ዕቃዎችዎን ቆልፈው ማስቀመጫ ትናንሽ
  ሳጥኖች

## የግል መጼዳጃ ክፍሎች

የግል መጸዳጃ ክፍሎች በቤተሰብ መገልገያ ማዕከሉ
ውስጥ ከመግቢያው በር ፊት ለፊት ይገኛል።
ክፍሉ ተለቅ ላሉ ልጆች፥ በጽኑ ለታመሙ ወጣቶ
ችና ልዩ እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች እን
ዲያገለግል በጥንቃቄ የተሰራ ነው። የገላ መታጠቢ
ያ የልብስ መቀየሪያ፥ ከፍ ዝቅ የሚሉ አልጋዎች
ና ለአካለ ስንኩላን የሚሆኑ ሽንት ቤቶችን የያዘ
ነው።

የግል መጸዳጃ ክፍሉ ከወላጆቻቸው ወይም ከርዳታ
ሰጪዎቻቸው ለመጸዳዳትና ለግል ጥንቃቄያቸው ር
ዳታን ለሚሹ ልጆችና እንዲሁም ለሌላ ያገለግላል።